ኢት-ኢኮኖሚ ET-ECONOMY

## የፌዴራልና የክልል መንግስታት የቢዝነስ ኢምፓየር በኢትዬጵያ

ፀ/ት ፂዬን ዘማርያም

**የፌዴራል መንግስትና የክልላዊ መንግስቶች የንግድ ኢንተርፕራይዝ** (Federal state and Regional states-owned enterprise (FRSOE)

**የኢትዬጵያ ኢኮኖሚ በሦስት ትልልቅ የቢዝነስ ሞኖፖሊዎች ቁጥጥር ስር ይገኛል፡፡**

{I}**የክልላዊ መንግስቶች የንግድ ኢንተርፕራይዝ** (Regional state-owned enterprise (SOE) sector)

**የህወሓት ፓርቲ የንግድ ድርጅቶች ትግራይ እንዶንምንት(ትእምት)፣የኢህአዴግ ፓርቲዎች፣የንግድ ድርጅቶችና ክልላዊ የልማት ድርጅቶች**(Regional development organizations and endowment-owned businesses)

{II} **የፌዴራል መንግስት ዘርፍ የንግድ ኢንተርፕራይዝ** (Federal state-owned enterprise (SOE) sector)

{III} **የግሉ ዘርፍ የንግድ ኢንተርፕራይዝ** (Private sector)

### {I} የክልላዊ መንግስቶች የንግድ ኢንተርፕራይዝ (Regional state-owned enterprise (SOE) sector)

**የህወሓት ፓርቲ የንግድ ድርጅቶች** ትግራይ እንዶንምንት (ትእምት) The Endowment Fund For The Rehabilitation of Tigrai (EFFORT)

አንደኛው በህወሃት የፖለቲካ ድርጅት የሃብት ቁጥጥር ስር የሚገኘው (ትእምት) የሚባል የንግድ ድርጅት በ1987 ሲሆን የዚህም የሃብት ምንጭ ህወሃት በሽፍትነት ለአስራ ሰባት ዓመታት ከኢትዬጵያ ህዝብ የዘረፈው ሃብት ነው፡፡ ኢፈርት ሁለት ክንፎች አሉት አንደኛው ክንፉ የኢንቨስትመንት መዓከል ሲሆን ሁለተኛው ክንፉ ደግሞ በጎአድራጎት ማዕከል ናቸው፡፡ የኢፈርት የኢንቨስትመንት መዓከል በ14 የተለያዩ ካንፓኒዎች የተደራጅ ናቸው፡፡በኢፈርት ሙሉ ውክልናና ኃላፊነት ተሰጥቶቸው ካንፓኒዎቹን የሚያስተዳድሩትና የሚመሩት ሼር ሆልደርስ ናቸው፡፡ የኢንቨስትመንት መዓከሉ ሁሉን ዓቀፍ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት (socioeconomic development) ሊያመጡ የሚችሉ በአስተዳደር ቴክኒክና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የሚጠቀሙ ምጡቅና ቅልጡፍ ሠራተኖች ማስማራቱን ይገልፃል፡፡

የህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት) የኢኮኖሚ ምሶሶ የሆነው ኢፈርት የቢዝነስ ኢምፓየር በኢትዬጵያ የግሉን ዘርፍ ባለኃብት በመቀናቀንና ሥራዎችን በመንጠቅ የሃገሪቱን ኃብት በሞኖፖል የሚቆጣጠር የህቡዕ ወይም ሚስጥራዊ ስውር ድርጁት ነው፡፡ የኢፈርት መሠረቱ የተጣለው በ1978 አ.ም ማሕበረ ረድኤት ትግራይ(ማረት) (Relief Society of Tigrai (REST) የህወሃት የገንዘብ ጃንጥላ፣ ሆኖ እንደ በጎአድራጎት ድርጅት በተቆቆመበት ግዜ ነበር፡፡ ምንም እንኮን ማሕበረ ረድኤት ትግራይ የጎአድራጎት ድርጅት ቢሆንም ቅሉ የሚመራው በህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ ማእከላዊ ኮሚቴ ነበር፡፡ በተለይ በርሃቡ ዘመን ከዓለም አቀፍ ኮሚኒቲውና ከውጭ ዲያስፖራ የሚጎርፍልትን የገንዘብ ድጋፍ ህወሓት የደርግን ወታደራዊ አገዛዝ ለመደምሰስ ትልቅ አስተዋፅዖ አድርጎለታል፡፡
የህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ በ1991እኤአ በትረ ስልጣኑን ከደርግ እንደተረከበ ማረት በእርዳታና መልሶ ማቆቆም ማስተባበሪያ ኮሚሽን በበጎ አድራጎት ድርጅት("NGO") ስም ተመዝግቦ የህወሓት መንግስት የገንዘብ ድጋፍ በጡጦ እየተጋተ ከአፍሪካ አህጉር ውስጥ በኃብት ትልቁ ኤንጂኦ ለመሆን በቃ፡፡ በ1995 እኤአ ህወሓት ለማረት ብረት መዝጊያና ጠንካራ አጋር ድርጅት መሠረተለት፣ትግራይ እንዶንመንት (EFFORT), የተቆቆመበት የኢንቨስትመንት የቢዝነስ ዶሴ ኢፈርት በሁለት ነጥብ ሰባት (2.7) ቢልዩን ብር መሆኑን ገልፆ በማግስቱ አንድ ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር መሆኑ ተገልፆል፡፡
ገብሩ አስራት የትግራይ ክልላዊ መንግስት ፕሬዜዳንት በመሆን ከ1991 እስከ 2001 እኤአ የህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴና ፖሊት ቢሮ እና የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ በመሆን ስርአቱን አገልግለዋል፡፡ የትግራይ ፕሬዜዳንት ሆነው ለአስር ዓመታት በነበሩ ግዜ ለክልሉ ያከናወኖቸው ዋና ዋና ሥራዎች መኃል ውስጥ የሚከተሉት ይገኛሉ፡፡ በኢፈርት ስር የተመሰረቱ፣ በ1990እኤአ የመሶቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ፣መስፍን ኢንደስትሪያል ኢንጅነሪንግ፣አዲግራት መድሃኒት ፋብሪካ እና አልሜዳ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ በእሳቸው አስተዳደር የተገነቡ ናቸው፡፡ እንዲሁም፣ አሉላ አባ ነጋ ዓለም አቀፍ የአይሮፕላን ማረፍያና፣ በክልሉ ውስጥ ብዙ መንገዶች አሠርተዋል፡፡ በ1993 የመቐሌ ቢዝነስ ኮሌጅ እና የመቐሌ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በኃላም በ2000እኤአ መቐሌ ዩኒቨርሲቲና የመቐሌ ኢንስቲቲዩት ቴክኖሎጂ እንዲሁም የግል ዩኒቨርሲቲዎች ተቆቁመዋል፡፡በኢትጵያ ውስጥ ሁለተኛ የሆነው፣በትግራይ ክልል ውስጥ የተመሠረተው አይደር ሪፈራል ሆስፒታልና የመቐሌ ዩኒቨርሲቲ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ በመሆን ያገለግላል፣ሆስፒታሉ 500 አልጋዎች ሲኖሩት 45 ስፔሻሊስት ዶክተሮች አሉት፡፡ በክልሉ ሌሎች መለስተኛ ስድስት ሆስፒታሎች ተሠርተዋል፡፡በማጠቃለያ በኢፈርት የተቆቆመው ድምፂ ወያነ ራዲዬ ስርጭቱን በትግራይ ክልላዊ መንግስት በማሰራጨት ለትግራይ ህዝብን ከሌላው የኢትዬጵያ ህዝብ ነጥለው እንዳስተዳደሩ በአጋዛዝ ዘመናቸው ከሌሎች ክልሎች መጥተው ትግራይ ውስጥ ተመድበው ይሰሩ የነበረ የመንግስት ሠራተኞች፣ መምህራን ከትግራይ ክልል እንዲወጡ አስደርገዋል፡፡ የትግራይ ክልል ከወሎ፣ ከአፋር፣ ከጎንደር ጉታ ገጠም መሬቶች ወደ ትግራይ እንዲከለሉ አድርገዋል፡፡ በክልሉ በእሳቸው ዘመን ምንም ዓይነት ነፃ ጋዜጣ አይገባም ነበር፡፡ የኢህአፓ አመራሮች በትግራይ እስር ቤቶች ታስረው፣ ተገርፈውና በጥይት ተደብድበው የሞቱት በእሳቸው አገዛዝ ስርዓት ነበር፡፡ ለህወሓት ሚስጥሩን ደብቀው ከ23 ዓመታት በኃላ በመፃሃፋ ሲገልፁ እሳቸው፣ ህወሓትና የህወሓት አንጃ አንድ ቀን በዚህ ወንጀላቸው እንደ ደርግ ለፍርድ መቅረባቸው አይቀርም!!! ያለፍርድ የተገደሉ የኢህአፓ ሠማዕትት የእናንተ በደም የታጠበ እጅ ከደርግ በምን ትለያላችሁ!!! ህወሓት የኢህአፓን ልጆች የኢህአሠን ሠራዊት በግፍ መግደላችሁ ሳያንሳችሁ ስልጣንም ይዛችሁ ያለፍርድ ዳግም ገደላችሁ!!! ለዚህ ምንም ይቅርታ አይኖረውም፡፡ ይሉኝታ የሌላችሁ የሥልጣን ጥመኞች፣ባወጣችሁት ህገ መንግስት ያለፍርድ ገደላ ፍርዱ ምን እንደሆነ አንብቡት፡፡አቤት! እንደ እባብ አፈር እየላሳችሁ መነሳት ስትችሉበት!!! እናንተ ቀሪ ህይወታችሁን ንስሃ ገብታችሁ ደብረ ዳሞ ብታሳልፉ ምን

አለ!!! አረ ስለ አብነ አረጋይ!!! ደርግ ሰዎች ረሽኖ በሬዲዩ የፍየል ወጠጤ አሰምቶ ስማቸውን በሬዲዩ በመጥራት ለቤተሰቦቻቸው ያረዳ ነበር!!! አንተም የእኛን ልጆች መረሸን በመፅሃፍህ አረዳህን፣ ወላድ ይፍረድብህ!!!በአንተ ልጅ ቢደርስና በዚህ መልክ የልጅህን ሞት ብትረዳ ምን ይሰማሃል። ይሄ ኢትዩጵያዊም ባህል አይደለም!!! በእነሱ ደም የተፃ መፅሃፍህ ብዙ ቀርሽ አወጣልህ!!! ሠማዕቱ ብዙ ኢትዩጵያዊ ደም መላሾች አላቸው፣ ህወሃትን የኢትዩጵያ ህዝብ አያምንም!!! የግዜ ጉዳይ እንጂ እናንተ ጠብም የላችሁ! አንድም፣ሁለትም፣ሦስትም ናችሁ!!! ተውኑ... አረ! ተውኑ ዘመናችሁ ሳያልቅባችሁ!!!
ገብሩ አስራት የትግራይ ክልላዊ መንግስት ፕሬዜዳንት ለ10 ዓመታት በነበሩበት፣ የፓርቲ ኃብት የሆኑ ጥገኛ ኢንተርፕራይዞች እንደ ኢፈርት ያሉ ያለ ጨረታ የመንግስት ፕሮጀክቶች ሥራ ይሠጣቸዋል፣ከባንክ የፈለጉትን ካፒታል ገንዘብ ያገኛሉ፣የመሠረተ ልማትና የአስተዳደር አገልግሎቶች፣የግብር እፎይታና ምህረት እንዲሁም ሌሎች የፖለቲካ ጥቅማ ጥቅሞች ድጋፍ ያገኛሉ። የኢኮኖሚ ዘርፎች፣ ዋነኛ የገንዘብ ምንጭ የሆኑ በግብርና፣በኢንደስትሪ፣በባንክ፣በማዕድን፣በኢንፖርትና ኤክስፖርት፣ በትራንስፖርት፣ በግንባታ ሥራዎች፣በኢንሹራንስና በመገናኛ ዘርፎች በፕራይቨታይዜሽን ኤጀንሲ በኩል ለእነዚህ የፓርቲ የመንግስት ጥገኛ መኸርገር ድርጁቶች እንዲሰጡ ተደርጎል። በቅርቡ ለራያ ቢራ ፍብሪካ ለጀነራል ፃድቃን ገብረትንሳኤ የኢትጵያ ንግድ ባንክ 960 ሚሊዩን ብር ብድር ሲፈቀድ እውን በስብሃትና ፃድቃን የጦር አበጋዞች ቡድን ፀብ አለን!!! ፍርዱን ለመከራ ገፈት ቀመሹ ለኢትዩጵያና የትግራይ ህዝብ እንተዋለን።

በ1995 እኤአ በህወሓት የተመሠረተው ትግራይ እንዶንመንት (ትእምት) የተቆቆመበት የኢንቨስትመንት የቢዝነስ ዶሴ ኢፈርት የተቆቆመበት የተከፈለበት ካፒታል  በሁለት ነጥብ ሰባት (2.7) ቢልዩን ብር መሆኑን ተገልፆ በማግስቱ አንድ ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር መሆኑን አበሰሩ።ኢፈርት ድርጅት በተለያ ግዜ የመሩት ጀነራል ማኔጀሮች (CEOs of EFFORT)

1- **ስዩ አብርሃ** Seeye Abraha, who left TPLF & EFFORT in 2001,
2- **ስብሃት ነጋ** Sebhat Nega, still a heavy weight in TPLF and CEO of EFFORT until 2008(?), and
3- **አባዲ ዘሙ** Abadi Zemu, former Ethiopian Ambassador to Sudan and CEO of EFFORT until 2012.
4- **ጌታቸው በላይ** (EFFORT is centrally managed by the Chief Executive Office, former Minister of Revenue, Getachew Belay.)
5- **አዜብ መስፍን** Azeb Mesfin, CEO of EFFORT until 2012-2014. እንደሆኑ ይታወቃል።

የህወሓት ፓርቲና ቢዝነስ (የንግድ ሥራ) እጅና ጎንት በመሆን የግሉን ዘርፍ ደፈጠጡት።በህወሓት መንግስት የቢዝነስና ፖለቲካ ግንኙነቶች ከ1990 እኤአ ጀምሮ በኢትዩጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ ከህወሓት/ኢህአዴግ ፓርቲዎች የተወረሱ ኃብቶች ኢፈርት በትግራይ፣ ጥረት በአማራ፣ ቱምሳ በኦሮሚያና ወንዶ በደቡብ ክልሎች ውስጥ እየተንሰራፉ መጡ።

## የማኑፋክአሪንግ ዘርፍ (Manufacturing Sector)

(1) **ሼባ የቆዳ ኢንደስትሪ** (Sheba Leather Industry) በ1993 እኤአ የተቆቆመው፣ ከመቀሌ ከተማ 45 ኪሌ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው ውቅሮ ከተማ ውስጥ ያለ ፋብሪካ ነው። ፋብሪካው የተከፈለ ካፒታል( paid up capital) አስር ሚሊዩን ዩኤስ ዶላር የተቆቆመ ሲሆን ለ670 ሠራተኞች የስራ እድል ፈጥሮል። ሼባ የቆዳ ኢንደስትሪ የበግና የፍየል ጥሬ ቆዳዎች በፋብሪካ አልፍቶና አዘጋጅቶ በመሸጥ ሥራም ላይ ተሠማርቶል። ሼባ የቆዳ ኢንደስትሪ ሁለት የምርት የማምረቻ ፋብሪካ ክፍሎች ሲኖሩት አንደኛው የጫማ ፋብሪካ ሲሆን ሁለተኛው የቆዳ ፋብሪካ ናቸው። የጫማ ፋብሪካ 1000 ጥንድ ጫማዎች በአንድ ፈረቃ ማምረት ይችላል።የጫማዎች ዓይነቶች የወንድና የሴት ጫማዎች፣ዘመናዊ ጫማዎችና ሰንደል ጫማ ይገኙበታል። የቆዳ ፋብሪካ ደግሞ 40000 ፊት ያለቀለት ቆዳ በሂደት አዘጋጅቶ ያቀርባል። የፋብሪካው ምርቶቹን የሚልክባቸው ሃገራቶች፣ በደቡብ ምሥራቅ ኤሽያ፣ምዕራብ አውሮፓና ሰሜን አውሮፓ ናቸው። ፋብሪካው ከውጭ ንግድ አጠቃላይ ትርፉ ከ10 እስከ 50 ሚሊዩን ዶለር ገቢ እንደአገኘ ከድረ-ገፁ መረዳት ይቻላል።የፋብሪካው ጀነራል ማኔጀር ገብረሚካኤል አረጋዊ ይባላሉ።
በኢትጵያ ሃያ ሁለት የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ፋብሪካዎችና በአዲስ አበባ፣ በኦሮሚያና አማራ ክልሎች ይገኛሉ። የግሉ ዘርፍ በሚደርስበት አድሎና ጫና የተነሳ ከነፃው የገበያ ውድድር አለመኖር የተነሳ ብዙዎቹ ለኪሳራ ተዳርገዋል። በአጠቃላይም በኢትጵያ 8000 ሠራተኞች በቆዳ ኢንደስትሪዎቹ ውስጥ ተቀጥረው ይሠራሉ። (Sutton and Kellow, 2010: 97). EFFORT’s Sheba Leathers, the only tannery in Tigray, started production in 2004, with a reported investment of ETB94million, and by 2006 had a skins processing capacity of around 4-5% of the national total, although this has apparently risen significantly since. An ETB300million expansion programme is ongoing, and the company aims to produce branded footwear and gloves with 70% going to the international market by 2020. Finished leather products currently account for only 15% of Ethiopia’s export earnings from the sector, and the government has put a series of taxes to discourage the export of unfinished hides and skins (Sutton and Kellow, 2010: 99). The company based in Wukro, north of Mekelle, employs 410 people.

(2) **መስፍን ኢንደስትሪያል ኢንጅነሪንግ** (Mesfin Industrial Engineering)



በኢፈርት የተቆቆመው፣መስፍን ኢንደስትሪያል ኢንጅነሪንግ በመቐሌ ከተማ በ1992 ዓ.ም በሰባት ሚሊዩን ብር ካፒታልና በ30 ሠራተኞች እንደተመሠረተ ይታወቃል፡፡ካንፓኒው በመቐሌ በ120000 ሽህ ሜትር ስኮየር ቦታ ላይ በ35000 ሜትር ስኮየር ቦታ ላይ የተገነባው ማኒፋክቸሪንግ ፋብሪካ ሲሆን በአዲስ አበባም 25 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በገላን ተመሳሳይ ቅርንጫፍ ፋብሪካ አለው ፡፡ በአሁኑ ግዜ ካንፓኒው 300 ሚሊዩን ብር ወይም 17.9 ሚሊዩን ዩኤስ ዶላር ካፒታል እንዳለው ተገልፆል፡፡ ካንፓኒው 800 ሚሊዩን ብር ወይም 47.6 ሚሊዩን ዩኤስ ዶላር የሚገመት ንብረት ሲኖረው 650 ቆሚ ሠራተኞች እንዲሁም 350 ግዚያዊ ሠራተኞች አሉት፡፡

መስፍን ኢንደስትሪያል ኢንጅነሪንግ ፣ለ3000 የጭነት መኪኖችና ተጓታች/ ተሳቢ አካሎችን በአገር ውስጥ በመስራት በሃገሪቱ ውስጥ ከ85-90 በመቶ የሚሆነውን ቢዝነስ ይቆጣጠራል፡፡ እንዲሁም ከ5 እስከ 10 ሚሊዩን ሊትር የሚይዙ የነዳጅ ታንከሮችና 1000 የጭነት መኪኖች የነዳጅና የውሃ ታንከሮች አካል ሰርተው በመግጠም ገበያውን ያለተቀናቃኝ ይዘዋል፡፡ ካንፓኒው በተጨማሪም Design, manufacture, supply and service of low bed and high bed semi-trailers and dry and liquid cargo drawbar trailers, erection of petroleum liquid reservoirs (including Electrical/ Instrumentation System), Supply & Erection of HVAC system, Steel Fabricated products for Industrial Application; and Vehicle Equipment Maintenance and Renting

መስፍን ኢንደስትሪያል ኢንጅነሪንግ የኤሌክትሮ ሜካኒካል ፋክተሪ ሥራ፣ የግንባታ፣ የመገጣጠምና የማደራጀት ስራዎችን ለመሰቦ የህንፃ መሣሪያዎች ማምረቻ ፋብሪካ፣አልሜዳ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካና ሼባ የቆዳ ኢንደስትሪ ፋብሪካ እንዲሁም በአማራ ክልል ጥረት የዳሽን ቢራ ግንባታና የቢራ ማቆሪያ ታንከሮች ያለጨረታ ስራ ተሰጥቶታል፡፡ ካንፓኒው በኢትዩ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት በሰሜኑ ግንባር የወታደራዊ ጨረታዎችን ያለአንዳች ተቀናቃኝ ተሰጣቸው፡፡ ካንፓኒው በትላልቅ ወታደራዊ መኪኖች የቢዝነስ ንግድ፣ በለስ የቀናው የኢፈርት የቦርድ ሊቀመንበር፣ የመከላከያ ሚኒስትርና የብሔራዊ ወታደራዊ ማዕከላዊ ዕዝ ኮማንድ ፖስት አመራር ከሰባቱ አንዱ በነበሩት ስዬ አብርሃ የመኪኖችና ወታደራዊ ተሽከርካሪዎች አጠቃላይ ጥገና ከተበረከተላቸው በኃላ ነበር፡፡ በኢትዩጰያ በግሉ ዘርፍ ተመሳሳይ ስራ ይሰሩ የነበሩ ስመ ጥሩ ካንፓኒዎች መኃል ማሩ ጋራዥ የመሳሰሉት በአድሎ እንዳይሰሩ ተጨናገፉ፡፡ በግሉ ዘርፍ የጭነት ትራንስፖርትና የነዳጅ ቦቴዎች ባለቤቶች ላይ ከኢትዩጵያ ንግድ ባንክ ብድር ለማግኘት የጭነቱን መኪኖች ቦዲ መቐለ መስፍን ኢንደስትሪያል ኢንጅነሪንግ ማሰራት ብድር የማግኘት መጀመሪያ ግዴታ ተጣለባቸው፡፡ አባቱ ዳኛ፣ ልጁ ቀማኛ ማለት አያንስም አንዱ የእናት ልጅ፣ አንዱ የእንጀራ ልጅ ሆኑ፡፡ Its vehicle-related business is widely thought to have been boosted during the period of the Ethio-Eritrean war (1998-2000), by a series of military contracts. Like a number of other EFFORT companies, MIE had the advantage of relative proximity to the northern battlefronts, and given its dominance of the sector, seems to have been the only domestic company with the capacity to take on this work. Observers have also noted that it also enjoyed a close connection with key figures in military procurement, when (Seeye Abraha) the then-Board Chairman of EFFORT and former Minister of Defence became a member of the 7-man national military Central Command.

መስፍን ኢንደስትሪያል ኢንጅነሪንግ፣አንኳር ስራዎች መኃል፤-

(ሀ)ለጢስ ዓባይ ሃይድሮፓወር ኤነርጂ ፕላንትና ለሌሎቹም ተቆማት፣ ውሃ ወደ ውስጥ የሚያስገባ መጋቢ ቧንቧ በመስራት ብዙ ኮንትራት ያለጨረታ ሠርቶል፡፡ (ለ) በ1990 እኤአ የአዲስአባባ ኤርፖርት ሠርቶል፣(ሐ) ካንፓኒው ስምንት የስኳር ፋብሪካዎች የኮንትራት ሥራዎች ሥራ አሰኪያጁና የህወሃት ፖሊት ቢሮ አባይ ፀሃዬ ያለጨረታ ተሰጥቶታል፡፡ (መ) በ2008እኤአ የኢትዩ-ጅቡቲ የባቡር መስመር ላይ የሚገኙ ድልድዩችን ለመጠገን የከፊል ኮንትራት ሥራ ከጣሊያኑ ኮስታ ካንፓኒ ጋር የ50 ሚሊዩን ፓውንድ የአውሮፓ ህብረት ፈንድ መርሃግብር ለመስራት ተዋውሎል በቀጣይም የኢትዩ-ጅቡቲ የባቡር መስመር የ5000 ኪሎ ሜትር ስራ ይጠብቃል፡፡(ሠ)ካንፓኒው በ2000እኤአ የራሽያ ሠራሽ ካማዝ መኪኖች መገጣጠም ጀምሮል (ረ) እንዲሁም በ2006 እኤአ የእርሻ ትራክተሮች መገጣጠሚያ ከህንድ ሚታል ካንፓኒ ንብረት የሆነውን ሶናሊካ ዓለም አቀፍ ስራ ተዋውሎል፡፡እንደ አዜብ መስፍን ገለፃ፣መስፍን ኢንጅነሪንግ 500 እጅ ሽያጩን መጨመሩና በሦስት እጥፍ ካፒታሉ እንዳደገ ገልፃለች፡፡''Similarly, Mesfin Industrial Engineering, the leading automotive firm in the nation, increased its sales by 500% and tripled its capital 3 times, according to Azeb Mesfin.''

### (3) መሰቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ (የህንፃ መሣሪያዎች ማምረቻ)(Messebo Building Material Production)



መሰቦ የሲሚንቶ ፋብሪካ በ1995እኤአ ከመቐለ 15 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የተመሠረተ ሲሆን ፋብሪካው የተቆቆመበት የተከፈለ ካፒታል 240 ሚሊዩን ብር ነው፡፡ የፋብሪካው ኢንቨስትመንት ካፒታል መጀመሪው መስመር 1.2 ቢሊዩን ብር እንዲሁም አዲሱ መስመር 2 ቢሊዩን ብር ወጪ ወጥቶበታል፡፡ ፋብሪካው በ2000 እኤአ ምርት ሲጀምር፣ ኦፒሲና ፕሮቲያን (OPC, protean cement) ሲሚንቶ ዓይነቶች አመረተ፡፡

**It was established with paid up capital of ETB 240 million. The first cement line of the factory was constructed by a Turkish based company ENKA with machines supplied by world renowned cement technology supplier FL Smidth of Denmark. The investment capital of the first line is around ETB 1.2 billion and the new line is about ETB 2 billion. The company started production of Ordinary Portland Cement (OPC) in April 2000.**

ፋብሪካውን የገነቡት የቱርኩ ኢንካ (ENKA) በማሽን ምርት አቅርቦትና ተከላ፣ እንዲሁም የዴንማርኩ ኤፊ ኤል ስሚትዝ( FL Smidth)እውቅ ሲሚንቶ ቴክኖሎጅ በሥራው ተካፍለዋል፡፡መሶቦ ፋብሪካ የሲሚንቶ ምርት 3,000ቶን በቀን፣900,000ቶን በአመት ማምረት ችሎታና ብቃት አለው፡፡ ካንፓኒው 1195 ቆሚ ሠራተኞች ሲኖሩት 240 ኮንትራት ሠራተኞችና 51 ጊዜያዊ ሠራተኞች አሉት፡፡ ፋብሪካው በኢትዩ-ኤርትራ ጦርነት ግዜ መጠነኛ ጉዳት ደርሶበት ነበር፡፡ ፋብሪካውን የቻይና ማኔጅመንት በኮንትራት ሲያስተዳድሩት ቆይተው በ2000እኤአ ውሉ ተቆረጠ፡፡ ፋብሪካውን እስከ 2003 እኤአ ድረስ

በኪሳራ ለመዘጋት ተቃርቦ ነበር ከዛም የፓኪስታን ማኔጆሮች ማስተዳደር ጀመሩ። በ2009 እኤአ መሶቦ ፋብሪካ የማስፋፍያ መርሃግብር ለቻይና ኮንትራክተር ሃንፌ (Hanfie)በ3 ቢሊዩን ብር ወይም 180 ሚሊዩን ዶላር እንዲሁም 141.6 ሚሊዩን ወይም 8.4 ሚሊዩን ዶላር ከDBE በመበደር ሲሚንቶውን ምርት 6000 ቶን በቀን ለማምረት ታቀደ።
መሰቦ የሲሚንቶ ፋብሪካ ሲቆቆም በደንበኛ ጥናት ላይ የተመሠረተ ባለመሆኑ ምክንያት ለብዙ አመታት በኪሳራ ለመስራት ተገዶል ። የፋብሪካው ርቀት በመላ ሀገሪቱ ምርቶቹን ለማከፋፈልና መሸጥ አልቻለም ነበር። በዚህም ምክንያት የህወሃት መንግስት ለመንግስት ፕሮጀክቶች መስሪያ ከመሶቦ ሲሚንቶ እንዲገዙ በማድረግ ኪሳራውን በህዝብ ኃብት አሸጋሽጎል። መሶቦ ፋብሪካ ምርቶቹን ለኢፈርት ንብረት ለሆኑት ትራንስ ኢትዩጵያና ጉና ማጎጎኘ ድርጅቶች በኩንታል 80 ብር እስከ አዲስአበባ ድረስ ያስከፍሉ ነበር። በግዜው የግሉ ዘርፍ የትራንስፖርት የጭነት ገበያው ዋጋ ከ50 እስከ 60 ብር በኩንታል ነበር። በህወሃት መንግስት የመሰቦ የሲሚንቶ ፋብሪካ ምርቶች ከትግራይ ወደ አዲስ አበባ፣ ቢኒ ሻንጉል ጉሙዝ ታላቁ የህዳሴ ግድብ ሥራ ሲሚንቶ በማመላለስ መሶቦ፣ ትራንስ ኢትዩጵያና ጉና ማጎጎኘ ድርጅቶች የጥቅሙ ተጋሪዎች ሆነዋል። ህወሓት የሚያሳዝነው በሃገር ሃብት እንዲህ መጠቃቀምና በኪሳራ ኢንቨስትመንት ስራዎች ሲሰሩ ምን ያህል የማህይሞች ሥራ ከመሶቦ ግድቡ ድረስ ሲሚንቶ በእጥፍ ዋጋ እየቀረበ እንደሆነ ልብ ይበሉ።

(4) አዲስ መድኃኒት/ፋርማሲዩቲካል ፋብሪካ (Addis pharmaceutical factory)



አዲስ መድኃኒት ፋብሪካ በ1992 እኤአ በሁለት ሰዎች በጋራ ንብረትነት የተመሠረተ የንግድ ድርጅት ነበር።ፋብሪካው ደቡብ ምዕራብ ትግራይ በአዲግራት ከተማ የተቆቆመ ፋብሪካ ነው። በ1995 እኤአ አንደኛው ሰው የንግድ ድርሻውን ለኢፈርት አስተለላለፈ። በ1997 እኤአ ፋብሪካው ምርት ማምረት በመጀመር 30 በመቶ ብቻ የማምረት አቅሙን እንደተጠቀመ ከዛም በህወሓት መንግስት ድጋፍ ከውጭ የሚገቡ መድኃኒቶች ወደሃገር ውስጥ እንዳይገቡ በማገድና ከአዲስ መድኃኒት ፋብሪካ እንዲገዙ ትእዛዝ በማስተላለፍ የመድኃኒት ገበያ ድርሻውን ከፍ ማድረግ ችለዋል። በአሁኑ ግዜ የፋብሪካው የምርት አቅርቦት 77 በመቶ መድረሱ ይገለፃል። ፋብሪካው ምርቱን 130 ዓይነቶች አድርጎ በመጨመርና በ10 የምርት ማምረቻ የመስመር ስርጭት (The company has more than nine production lines and fully equipped laboratories as well as the capacity to produce tabulates, capsules, syrups/suspensions, dry powders for reconstitution, injectable vials, liquid injectable ampules, creams and ointments.)በማድረግ በኢትዩጵያ ትልቁ የመድኃኒት ፋብሪካ ለመሆን በቅቶል። Addis Pharmaceutical Factory manufactures more than 91 high quality products of different therapeutic categories including antibiotics, gastro-intestinal drugs, central nervous system drugs, cardiovascular drugs, anti-diabetic agents, antihistamines, antehelmitics, analgesics, antiprotozoals, respiratory drugs, dermatological preparations, minerals and vitamins as well as large volumes of Parentals. በ2009 እኤአ ሁለተኛውን ፋብሪካውን በአቃቂ ከተማ manufacturing of large volumes Parenterlas.

The Ethiopian pharmaceuticals sector remains relatively small, with 10 firms producing pharmaceutical products, and three others making medical supplies. The largest of these are MIDROC's Pharmacure, the SOE EPHARM established in 1972 (currently 50 products and 570 employees), and EFFORT's Addis Pharmaceuticals. Ethiopian production satisfies only
20% of the domestic market: pharmaceuticals imports were valued at US$190million in 2008, and more than a hundred importers and wholesalers are registered in the country.

Although the sector is regarded as a priority for development and import substitution, tight regulation constitutes a barrier to entry, as does the Ethiopian industry's import of more than 90% of raw materials, accounting for 40% of costs (Sutton and Kellow, 2010 165ff). A number of medium- sized enterprises were reported to be in trouble in the middle years of the decade….Controversy attaches to the eventual purchase by EFFORT in 2005 of the shares of the remaining partner, after relations apparently soured (see below, on Tower Trading Company). …Addis Pharmaceuticals also hopes to move into regional export markets, and its horizontal integration was improved by the acquisition of the newly established but insolvent Lifeline IV fluid manufacturer. Ninety-eight per cent of the company's raw materials are imported, mainly from China, and 70% of its products are sold to the state-owned Pharmaceutical Fund Supply Agency on open-tenders (Sutton and Kellow, 2010). እንደ አዜብ መስፍን ገለፃ፣አዲስ መድኃኒት ፋብሪካ አራት ግዜ መነሻ ካፒታሉን እንደበላና በባንክ ቁጥጥር ስር እንደነበር፣ በአሁኑ ግዜ ግን 900 ሚሊዩን ብር የተቆለለ እዳውን እደከፈለና በአመት ውስጥ ብድሩን እንደሚጨርስ ገልጻለች።‹‹Addis Pharmaceuticals Production, a gigantic firm located in Adigrat, eastern Tigrai, had "eaten" its capital four times and has been under the lending bank, according to Azeb Mesfin. However, now, she claimed, it paid off about 900 million birr accumulated debt and it is poised to finish its debts within a year, thus fully returning to EFFORT's folds.››

(5) አልሜዳ ጨርቃጨርቅ (Almeda Textile)



አልሜዳ ጨርቃጨርቅ በ1996 እኤአ በአድዋ ከተማ በኢፈርት የተመሠረተ ድርጁት ነው፡፡ ፋብሪካው ዘመናዊ የጨርቃጨርቅ፣የተለያዩ አልባሳቶች ያመርታል፡፡ ፋብሪካው የጥጥ ማዳወሪያ፣የመፍተያ፣የማቅለሚያና ሁሉን አቀፍ የአልባሳት ማምረቻ ያካተተ ሲሆን የሲዊስ፣ሆላንድ፣የጀርመንና የጣሊያን ስሪት ማሽኖች ተገጥመውለታል፡፡Almeda Textile Factory has a yearly production capacity of 7,020 tonnes of yarn, 16,751,100mt.of grey fabric, 15,387,000mt.of processed fabric, and about one million pieces of basic shirt equivalent garments. የፋብሪካ የግንባታ ወጭ 94 ሚሊዩን ዩኤስ ዶላር ነበር፡፡ አልሜዳ ፋብሪካ 3600 ሠራተኞች በመቅጠር በዘርፍ በሦስት ፈረቃ ሠራተኞች ያሰማራ ካንፓኒ ለመሆን በቅቶል፡፡ ፋብሪካው በ2007/08 እኤአ 14.6 ሚሊዩን ዶላር ያለቁ ምርቶች ወደውጭ በመላክ ገቢ አግኝቶል፡፡ የጥጥ ጥሬ እቃ በሃገር ውስጥ ማነስ ምክንያት በሃገር ውስጥ የሚመረጥ ጥጥ ወደ ውጭ ገበያ እንዳይላክ በመንግስት አሳግዶል፡፡ ፋብሪካው ምርቱን ወደ ውጭ በመላክ ከፍተኛ ገቢ ለማግኘት ቢጥርም በዘርፍ በተሰማሩ የቻይናና የቱርክ የጨርቃጨርቅ ፍብሪካዎች የምርት የመሸጫ ዋጋ ጋር በዓለም አቀፍ የገበያ ውድድር መወዳደር አልቻለም፡፡ፋብሪካው ባለበት የማኔጅመንት ችግር ፋብሪካውን የሚያስተዳድሩት አንዴ የቻይና(Chinese management company) እንዲሁም የፓኪስታን (Moonlight)እና ቀጥሎም (Tradesman) ሲያስተዳድሩት ቢቆዩም ካንፓኒው እስከ 2010እኤአ ትርፋማ ሊሆን አልቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት በባንክ ባለበት ከፍተኛ ብድር ለመዘጋት ተቃርቦ የነበረ ቢሆንም በህወሃት መንግስት ድጋፍ እየተንገዳገደና እየተገራገጨ በሦስት እግሩ የቆመ ፋብሪካ ሆኖል፡፡

''Reflecting the high government priority placed on boosting this sector,credit is reported to have been relatively easily available, to state, private, and foreign investors alike. Almeda's plant cost more than US$94million. Since its foundation the company has struggled for profitability in a context of management and skills weaknesses, low global cotton prices, and cutthroat import competition. Located close to the Eritrean border, it was hit particularly hard during the Ethio-Eritrean war, a few years after which it was rumoured that the banks would foreclose on the company's heavy loans. Management problems saw the involvement of a Chinese management company, later a Pakistani company (Moonlight) and most recently from 2006 a second Pakistani management company (Tradesman). Almeda was reportedly the only one of EFFORT's companies still not turning a profit at the end of 2010 (interview). .'' እንደ አዜብ መስፍን ገለፃ፣አልሜዳ ጨርቃጨርቅ ለአለፍት 15 አመታት ከባድ ኪሳራ ውስጥ እንዳለ አንድ ቢሊዩን ብር እዳ እንዳለበት ገልፃ ግማሹ እዳ እንደተከፈለ ሆኖም የፋብሪካው መሽኖች ያረጁና አገልግሎታቸውን የጨረሱ እንደሆነ ገልፃለች፡፡ አሮጌ ማሽን አስገጥሞ ማልቀስ!!! የምታወራውን ታውቀው ይሆን ከማለት በስተቀር አንባቢ የሙሰናውን ደረጃ እራሱ ይፍረድ፡፡''Nonetheless, Almeda Textile Factory didn't improve as fast as planned, Azeb Mesfin noted. She elaborated the firm has been suffering losses for the past 15 years – which is since its establishment. It had over one billion birr in debts when she assumed EFFORT's chief post. So far, about half of the debt has been paid off. She added "we started paying debts at the time when the firm reached obsolescence (meaning: the firm was old enough to regain its initial capital and start replacing its machines)". According to Azeb Mesfin, the firm paid neither the principal nor the interest on its debts for 15 years.''

## የአገልግሎት ዘርፍ (Services Sector)

### {1}ትራንስ ኢትዩጵያ (Trans Ethiopia)





ትራንስ ኢትዩጵያ ኃ/የ/የ/ማ በ1993 እኤአ በኢፈርት በተከፈለ ካፒታል 100 ሚሊዩን ብር የተቆቆመ ድርጅት ሲሆን የደረቅና የፈሳሽ ጭነቶችን በትራንስፐርት አገልግሎት ዘርፍ ለማመላለስ፣እንዲሁም ከውጭ ሃገር ጎማ ፣ባትሪዎች፣የመኪና ቅባት መሳሰሉትን አስመጥቶ ለማከፋፈልና ለመሸጥ እንዲሁም ከሦስተኛ እስከ አምስተኛ መንጃ ፍቃድ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ መሣሪዎችን በመጠቀም ስልጠና መስጠት በሚል ሥራ ጀመረ፡፡ ከ2009እኤአ ጀምሮ ትራንስ ኢትዩጵያና ኤክስፐሬስ ትራንዚት ስርቨስ ኢንተርፕራይዝ( Express Transit Service Enterprise) ጋር ሽርክና በመፍጠር የጭነት የትራንስፐርት አገልግሎት፣ የዕቃ ማመላለስ/ማጎጎዝ አገልግሎት፣የጉምሩክ አገልግሎት፣እንዲሁም የመኪና ጎማዎች( Pirelli tyres)፣ ባትሪዎች (Japan Star Batteries) ፣ ሎሎች ተመሳሳይ ቢዝነስ ለመስራት ካፒታላቸውን 102.5 ሚሊዩን ብር ከፋ በማድረግ በጋራ ለመስራት ተስማሙ፡፡ የካንፓኒው ዋና ፅሕፈት ቤት መቐለ ሲሆን ቅርንጫፍ ፅህፈት ቤቶች በአዲስአበባ፣ ናዝሬት፣ ሚሌ፣ሁመራ፣ኮምቦልቻ፣ጎንደርና ጅቡቲ ከፈተ፡፡ ካንፓኒው፣የውጭ ንግድና የገቢ ንግድ የሚወጡና የሚገቡ ምርትና ሸቀጣሸቀጦችን በደረቅና ፈሳሽ ጭነት የትራንስፐርት አገልግሎቶች በማመላለስ በቮልቮ፣አይቪኮ፣ስካኒያና ሲኖ የጭነት መኪኖች ይጠቀማሉ፡፡ ካንፓኒው ከትግራይ ረድኤት ድርጅት ጋር በመሆን የደረቅና የፈሳሽ ጭነት የትራንስፐርት አገልግሎትና የመኪኖች የጋራዥ አገልግሎት በ458 ጭነት መኪና ከነተሳቢውና በ23 የፈሳሽ ጭነት መኪኖች ይጠቀማሉ እንዲሁም የእቃ ማስቀመጫ መጋዘኖች በኪራይ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ካንፓኒው 1248 ሠራተኞች አሉት፡፡

TransEthiopia operates alongside a series of public and private transport companies, and around 90 cooperative-style transport associations, of which 20 operate fleets of between 100 and 400 vehicles, in a market where transport unit costs have been declining. The total national transport capacity in 2006 was estimated at over 43,000 vehicles, of which two thirds were available for commercial hire: 35,600 for dry cargo, and 1,800 for liquid cargo. TransEthiopia is reported regularly to subcontract 30-40% of its business to a number of transport associations, significantly leveraging its market share. It also subcontracts 'gomista' (tyre repair), and loading/unloading services to small associations in Mekelle, Adama and Mille. Whilst the dry cargo sector shows little concentration at the national level (regional markets may be different), the transport

of liquid cargo is more concentrated, with the top 8 operators (of which TransEthiopia is one) having 67% of lifting capacity, according to Transport Authority figures. TransEthiopia has long been considered one of the most profitable arms of EFFORT, and claims an exemplary record in timely, even early, repayment of credit (including loans of ETB100million and ETB35million from Dashen Bank, and ETB150million from the CBE,
equivalent to US$5.9million, US$2million, and US$8.9million respectively). Its position in the transport sector in the 1990s was considered to be controversially dominant, particularly in relation to the lucrative long-haul transport of relief grain from the ports to Northern Ethiopia. TransEthiopia's commercial incorporation of several hundred Mercedes and IVECO truck- trailers donated on a humanitarian basis to REST during the 1980s, and its ongoing role moving large quantities of humanitarian cargo for the organization, gave it an early competitive advantage. Competitors complained that high prices paid for food distribution to remote rural centres in Tigray and Amhara allowed TransEthiopia to offer unmatchable long-haul rates. EFFORT and REST responded to critics by insisting that market forces alone would provide inadequate protection to the high transport capacity to remote areas in the north of the country needed in times of food insecurity. TransEthiopia's involvement in the transport of fertilizer throughout the country during the 1990s is also thought to have been highly profitable, and it is clear that the business has well established ongoing client relations both with its EFFORT sister companies, and in the sugar, fertiliser, imported cement, and humanitarian cargo sectors. **እንደ አዜብ መስፍን ገለፃ፣ትራንስ ኢትዩጵያ ለአለፍት 20 አመታት የሂሳብ ደብተሩን ኦዲት እንዳላስደረገ ሆኖም የካንፓኒው ካፒታል 270 ሚሊዩን ብር እንደሆነና ቅርብ ግዜም 2 ቢሊዩን ብር እንደደረሰ ገልፃለች። በዚች ዓይነት የፖለቲካ ሥራ አስኪያጅ ተመርቶ እንዴት ትርፋማ መሆን ይቻላል!!! ስንት የተማረ ባለባት ትግራይ ከማለት በስተቀር ምን ይባላል!!!**

Azeb Mesfin also indicated that the transport giant Trans-Ethiopia has not been growing as fast as it should for years. However, in the past years, the firm's capital grew two or three times and managed to close its 20 years backlogs of accounting books. She added, its capital was 270 million "recently" and now reaching 2 billion birr.

## {2}ኤክስፕሬስ ትራንዚት ሰርቪስ (Express Transit Service)

**ኤክስፕሬስ ትራንዚት ሰርቪስ ካንፓኒ በኢፈርት በ1995እኤአ ሲቆቆም በ30 ሚሊዩን ብር ካፒታል የተመሠረተ ድርጅት ነው። ካንፓኒው ከሚሰጣቸው የኪራይ አገልግሎቶች ውስጥ አጠቃላይ የመጋዘን ቦታዎች ለካርጎና ለኮንቴይነሮች ማስቀመጫ ስፍራ ማደራጀት፣ እንዲሁም ካንፓኒው የራሱ የጭነት መኪኖች በማዘጋጀት የትራንስፖርት አገልግሎት ከጅቡቲ ወደብ ወደ ኢትዩጵያ በማመላለስ ከፍተኛ የገበያ ድርሻ በዘርፍ እንዳለው ይገልፃል። ካንፓኒው ዋና ቢሮና አስር ቅርንጫፍ ቢሮዎች በሃገሪቱ ውስጥ አሉት።**
**ኤክስፕሬስ ትራንዚት ሰርቪስ ፖርት ሱዳን ወደብን ተጠቃሚ ብቸኛ ትራንዚት ካንፓኒ ነው። ካንፓኒው የዓለም አቀፍ ትራንስፖርት ድርጁት አባል ነው። ካንፓኒው ትራንዚት ሰርቪስ በግሉ ዘርፍ የአንበሳውን ድርሻ እንዳለውና በመንግስታዊ፣ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ብዙ ደንበኞች እንዳሉት በድረ-ገፅ ላይ ገልፆል።**

- Extran is the only transit company that managed to enable Ethiopia to utilize Port Sudan.
- The sole member of the GTO (Global Transport Organization) in Ethiopia, which is networked to 154countries or 750cities around the world.
- It has already attained the leading share, as compared to private competitors in the sector, consequential of its capability to amass a long list of clientele ranging form prominent private companies, governmental, non-govern-ment and international organizations. To list few of the long-standing customers from each category. .........More >>

## {3}ጉና ትሬዲንግ ሀውስ ኮንስትራክሽን(Guna Trading House Construction)



**ጉና ትሬዲንግ ሀውስ ኮንስትራክሽን በ1992 እኤአ በኢፈርት የተቆቆመ የንግድ ድርጅት ሲሆን በ10 ሚሊዩን ዩኤስ ዶላር ካፒታል የተመሠረተ ነበር። በአሁኑ ግዜ በአመት የሚያንቀሳቅሰው ገንዘብ** ( annual turn over)

60 ሚሊዩን ዩኤስ ዶላር እንደሆነ ተገልፆል። በ2005/6 እኤአ 170 ሚሊዩን ብር የነበር ሲሆን በ2008/9 እኤአ 796 ሚሊዩን ብር ደርሶል።በአሁኑ ግዜ 1ቢሊዩን ወይም 60 ሚሊዩን ዶላር በአመት እንደሚያንቀሳቅስ ተገልፆል።

ካንፓኒው ዋና ቢሮው አዲስአበባ ገርጂ ሲሆን ቅርንጫፍ ቢሮዎች በመቐለ፣ሽሬ፣ሁመራ፣ደሴና ጎንደር ከተሞች ውስጥ ይገኛሉ። በአሁኑ ግዜ ዋና ቢሮውን በ15 ሚሊዩን ብር ወጭ በማስገንባት ላይ ይገኛል።

ጉና ትሬዲንግ ሀውስ የውጭና ገቢ ንግድ ስራ ላይ የተሠማራ ካንፓኒ ነው። በውጭ ንግድ ከሚልካቸው የግብርና ምርቶች መኃል ሰሊጥ፣የተፈጥሮ ሙጫ፣ቡና፣ጥራጥሬና ቅመማ ቅመሞች፣የቅባት እህሎች ይገኙበታል። በገቢ ንግድ የሚያስመጣቸው የግንባታ ዕቃዎች፣ኢንደስትሪ ግብዓቶች ውስጥ የግንባታ ፌሮ ብረት፣መስተዋት፣ጎማ፣ወረቀትና የግብርና ግብዓቶች ልዩ ልዩ ማዳበሪያ እንዲሁም የማከፍፈል ሥራዎችን ይከውናል። ካንፓኒው አጠቃላይ ትርፍ በ2002/03 እኤአ 4 ሚሊዩን ዩኤስ ዶላር የነበረ ሲሆን በ2006/07እኤአ 1.22 ቢሊዩን ኤስ ዶላር በማደግ ከበፊቱ ጋር ሲነጻጸር 227 በመቶ ከፍ ብሎል። የካንፓኒው ወደ ውጭ የሚልከው ሽያጭ በ2002/03እኤአ 3.5 ሚሊዩን ዩኤስ ዶላር የነበረ ሲሆን በ2006/07እኤአ 11 ሚሊዩን ዩኤስ ዶላር ነበር በ214 በመቶ አድጎል። በአጠቃላይ የካንፓኒው አጠቃላይ ሽያጭ በዚሁ አመት ውስጥ ከ14 ወደ 43 ሚሊዩን ዩኤስ ዶላር የነበር ሲሆን፣በ200 በመቶ እጅ አድጎል። በአለፉት አምስት አመታት ውስጥ በአጠቃላይ 33.6 ሚሊዩን ዩኤስ ዶላር ከሰሊጥ ገቢ አግኝቶል።በአሁኑ አመት ብቻ ካንፓኒው 20000ቶን ሰሊጥ ወደ ውጭ በመላክ 38 ሚሊዩን ዩኤስ ዶላር አግኝቶል። ይህም የሆነው በዓለም አቀፍ ገበያ የሰሊጥ ምርት ከ900 ወደ 2000 ዩኤስ ዶላር በቶን ከፍ በማለቱ ነው።

በኢትጵያ 36 ካንፓኒዎች የቅባት እህሎችና ጥራጥሬዎች ወደ ውጭ ሃገር የሚልኩ ሲሆን ዋነኛው ላኪ ጉና ትሬዲንግ ሀውስ ነው።ካንፓኒው ለሳውድ አረቢያና ቱርክ የቅባት እህሎች ይልካል በ2008/9እኤአ 180 ሚሊዩን ዩኤስ ዶላር ገቢ በኢፈርት ድርጅቶች የአንደኛ ደረጃ አግኝቶል። በዚሁ ግዜ ትራንስ ኢትዩጵያ 80 ሚሊዩን ዩኤስ ዶላር ገቢ በማግኘት የሁለተኛ ደረጃ አግኝቶል። እንዲሁም በሃገሪቱ በግሉ ዘርፍ ኤክስፖርት በማድረግ፣የተሰማሩ 60 ካንፓኒዎች የቡና ምርት ወደ ውጭ ሃገር የሚልኩ መሆናቸው ይታወቃል። በኢትዩጵያ በቀ.ኃ.ሥ ዘመን የጀመሩ የግሉ ዘርፍ ባለኃብት በዚህ መንገድ ነው ከንግዱ ጫዋታ የወጡት። ቀሪውን ለአንባቢው ህሊናና ፍርድ መተው በቂ ነው።

Coffee is Ethiopia’s most valuable export commodity, accounting for 35% of foreign exchange earnings, and 25% of GDP (Sutton and Kellow, 2010: 33). Oilseeds and pulses constitute Ethiopia’s second largest export commodity after coffee, and in 2008/9 export revenue reached US$445million (Sutton and Kellow, 2010:)

Both sets of commodities are now traded under the Ethiopian Commodities Exchange (ECX), established in 2008, in order to improve the efficiency of trading of a range of agricultural products. ECX has had a significant impact on the way in which import-export companies interact with producers, improving market information for producers, but also introducing an intermediate mechanism. Teething problems with the establishment of ECX’s storage and transport logistics in the Humera/Shire area are projected to have a significant impact on Guna’s flagship export of sesame during the current financial year. The intervention of ECX in the oilseeds sector has driven significant changes in the relationships between producers, including the EFFORT sister company Hiwot Mechanised Agriculture, and buyers including Guna. Guna, along with its sister endowment-owned companies in other parts of the country (Ambassel, Dinsho, and Wendo), was criticised for an aggressively competitive approach to the fertiliser import market during the 1990s. Private operators were first allowed to enter the state-controlled fertiliser market in 1993, and price controls and subsidies were lifted in 1996.

It seems clear that the links between organisations with strong connections to EPRDF and the government in the supply and distribution of fertiliser in the 1990s went well beyond a normal pattern of commercial synergies. Fertiliser in Tigray, for instance, was for some time imported and distributed by Guna, transported by TransEthiopia, on roads constructed by Sur, under an extension programme organised by REST, on credit provided by the Dedebit Savings and Credit Institution (DESCI), through Farmers’ Associations and Co-operatives, with a payment guarantee from REST and/or the regional government.

Since the beginning of the century, the SOE Agricultural Inputs Supply Enterprise (AISE) has once again increased its market share, and since 2005, co-operatives have become involved in fertiliser supply, greatly reducing the involvement of endowment-owned companies, particularly Guna. Guna’s decision to move into coffee exports in 1999 was also controversial, denoting its willingness to compete with its sister endowment-owned companies to trade a commodity grown in Oromia and the SNNPRS. Guna’s more recent move into construction materials, particularly re-bars, reflects the demands of the construction boom of the period from 2004

Guna Trading is a shareholder in United Insurance, whose CEO is a trenchant critic of business policy.

## {4}ሱር ኮንስትራክሽን (SUR Construction)

ሱር ኮንስትራክሽን በ1992 እኤአ በ180 ሚሊዩን ብር መነሻ ካፒታል በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የተመሠረተ ካንፓኒ ነው። በ1995 እኤአ በኢፈርት ድርጅት ሥር ሆኖ በ2003 እኤአ ኃ/የ/የ/ድርጅት ሆኖ በኢፈርት ሥር ተዋቀረ። ሱር ኮንስትራክሽን በአሁኑ ግዜ አንድ ቢሊዩን ብር ወይም 60 ሚሊዩን ዩኤስኤ ዶላር ንብረት ያለው ድርጅት ነው። የሱር ካፒታል 200 ሚሊዩን ብር ወይም 12 ሚሊዩን ዩኤስኤ ዶላር ከፍ ብሎል። የሱር አመታዊ ተንቀሳቃሽ ገንዘብ 690 ቢሊዩን ብር ወይም 41 ሚሊዩን ዩኤስኤ ዶላር ደርሶል።ሱር በአሁኑ ግዜ የሚሰራቸው ፕሮጀክቶች ዋጋ 3.5 ቢሊዩን ብር እንደሚገመት ኢፈርት አስታውቆል። ሱር ኮንስትራክሽን በሃገሪቱ ውስጥ ያለው በግንባታው ዘርፍ ያለው የገበያ ድርሻ 10 በመቶ ይዞል። ሱር ኮንስትራክሽን 1000 የግንባታ ማሽነሪዎችና ፕላንት ሲኖሩት እንዲሁም 1500 ቆሚ ሠራተኞችና 6000 የቀን ሠራተኞች እንዳሉት ኢፈርት በ2010እኤአ ገልፆል። Sur Construction was established as a share company in January 1992 with an initial capital of ETB180million, and is based in Addis Ababa. Brought under EFFORT in 1995, and reorganized as a PLC in 2003, it now has assets valued at around ETB1billion (US$60million), and capital of ETB200million (US$12million). Its annual turnover is more than ETB690million (US$41million), with a recently estimated cumulative project value of more than ETB3.5billion (EFFORT, n.d.[2010a]). The company estimates its market share of the construction sector at around 10%.

The company has almost 1,000 pieces of construction machinery and plant, and employs more than 1,500 permanent and contract staff, and 6,000 daily labourers (EFFORT, n.d.[2010a]).

ሱር ኮንስትራክሽን በግንባታው ዘርፍ ከአከናወናቸው ስራዎች ውስጥ

(ሀ) በሃይድሮ ኤሌትሪክ ፓወር ፕሮጀክቶች ግንባታ ሥራዎች በጢስ አባይ(በአማራ ክልል)፣ በተከዜ (ትግራይ ክልል) ውስጥ ከሰርቢያንና ከቻይና ኮንትራክተሮች ጋር አብሮ ያለጫረታ ሠርቶል።

(ለ)የኤርፖ`ርት ግንባታ ላሊበላ(በአማራ ክልል)ና፣በሁመራ(የጎንደር መሬት በምስራቅ ትግራይ የተከለለ)ያለጫረታ ሠርቶል።

(ሐ) በኪኑ-ሕንፃ ግናባታ፣የመቐለ ዩኒቨርሲቲ፣አክሱም ዩኒቨርሲቲ፣(ትግራይ ክልል)፣አልሜዳ ጨርቃጨርቅና የልብስ ፋብሪካ፣ በመቐለ የሰማእታት ሃውልት እንዲሁም በአዲስአበባ የስፖ`ርት ኮምፕሌክስ ከኢንፔሪያል ሆቴል አጠገብ ገንብቶል።ለትግራይ አንጋፋ የጦር ጉዳተኞች ማሕበር በአዲስአበባ ስታዲየም ትልቅ ፎቅ ገንብቶል፣ለትግራይ ረድኤት ድርጅትና ትግራይ ልማት ማሕበር ዋና ፅህፈት ቤት በመቐለ ከተማ ትልቅ ፎቅ ገንብቶል። እንዲሁም በቬርኔሮ ኮንስትራክሽን ካንፓኒ ጋር አዲስአበባ ቦሌ ክፍለከተማ ውስጥ ሜጋ ኔት ኮርፖ`ሬሽን የኢፈርት ዋና ፅህፈት ቤት ሕንፃ ገንብቶል። Sur construction built a building for the Tigray Veteran Fighters Association, with funds made available by EFFORT; as well as HQ buildings for REST and TDA in Mekelle (it is notable that the Mega-NET corporation building in Addis Ababa's Bole, which houses the EFFORT office in Addis, was built by the long-established Ethiopian-Italian contractor Varnero).

(መ) በመንገድ ግንባታ ዘርፍ፣ሱር ኮንስትራክሽን የሰራቸው መንገዶች ከጎንደር-ዳንሻ 138 ኪሎ ሜትር፣ከአርባምንጭ-ጂንካ 112 ኪሎሜትር፣ ከሆለታ-ሙገር 57 ኪሎሜትር፣ ከወረታ- ጎንበ 49 ኪሎሜትር ሠርቶል የመንገድ ሥራው ወጭ አልተገለፀም። በተጨማሪም ሱር ኮንስትራክሽን በንዑስ ኮንትራክተርነት በአነስተኛ የመንገድ ስራ በመሳተፍ፣ 10 ሚሊዩን ብር በምስራቅ ደደቢት እና በፊንጫ በምስራቅ ኦሮሚያ 20 ሚሊዩን ብር መንገድ ገንብቶል። ሱር ኮንስትራክሽን ያጋጠመውን የንግድ ጨረታ የማሸነፍ ችግርና ከባንክ ብድር የመግኘት ችግሮች ህጋዊና የሥነ ምግባር ደረጃን ያለውን ቅሬታ በሚቀጥለው ሁኔታ ገልፆታል።

''The company reports that it faces difficulties both in winning bids and in securing credit, because of what it claims is its 'exemplary' commitment to legal and ethical business standards. Examples of unsuccessful bids in 2008, for instance, reportedly include those for road construction on Arerti-Gobensa (Mojo-Metahara in Oromia), Yalo-Chercher-Mehoni (in Tigray/Afar), Endaselassie-Dedebit (in Tigray), and Sanja-Keraker (in Amhara, to the Sudan border), all of which were awarded to competitors. A loan of ETB100million secured from the CBE in 2008/9 represents 10% of Sur's assets, and reportedly took 6 months to secure. Sur represents a key component of the strong integration that characterises the EFFORT group of companies, as well as other closely associated organizations in Tigray.'' እንደ አዜብ መስፍን ገለፃ፣ሱር ኮንስትራክሽን በአለፉት 15 አመታት ውስጥ፣ ለሁለት ግዜ መነሻ ካፒታሉን እንደበላና አሁን እንዳገገመ ገልፃለች። በትግራይ ህዝብ ስም ዘረፍነው፣ ሰረቅነው፣ ገንዘቡን ባህር ማዶ አሸሽነው ብትይ አይሻልም!!!The CEO cited the indicated in her interview that one of the major firms, Sur construction, which had "eaten" its capital twice in the last fifteen years, have now fully recovered and eyes on expansion projects.

## {5}ሮማናት (Romanat)

ሮማናት በ2009እኤአ በኢፈርት የተቆቆመ ድርጅት ነው። ሮማናት በዚሁ አመት ልዩ ልዩ ተጣጣፊ የዕቃ ማሸጊያ ካርቶኖች፣ፖ`ሊፕሮፕሊን ቦርሳ/ጆንያ ለአግሮ ፕሮስሲንግና ማኑ-ፋክቸሪንግ ማሸጊያ ምርቶች ማምረት ጀምሮል። የሮማናት ካንፓኒ ደንበኖች የሆኑ የኢፈርት ድርጅቶች ለመሶቦ የሲሚንቶ ማሸጊያ፣ ለሼባ፣ ለትራንስኢትጵያ፣ጉና እንዲሁም ለብዙ ዱቄት ፋብሪካዎች ምርት ማሸጊያ ሠርቶል። ሮማናት 260 ሠራተኞች አሉት። ሮማናት የእቃ ማሸጊያ ካንፓኒ በጉምሩክ አስራርና በአበዳሪ ባንኮች ያለውን ቅሬታ ያንቡት።

''Similarly materials required to establish Romanat Packaging were delayed in a container for more than a year, because of difficulties with customs clearance. EFFORT companies have sought and obtained credit from a range of public and private banks, not only from the state- owned banks or Wegagen Bank, in which they have shares. Financial sector linkages are not only in-house: Guna Trading is a shareholder in United Insurance, whose CEO is a trenchant critic of business policy.''

## {6}ታወር ትሬዲንግ ካንፓኒ (Tower Trading Company)

ታወር ትሬዲንግ ካንፓኒ ወይም ሰናይ ትሬዲንግ ካንፓኒ በ1993እኤአ በኢፈርት በታላቆ ብሪታንያ፣በሎንዶን ከተማ በሼር የተቆቆመ በተከፈለ ካፒታል ሦስት መቶ ሽህ ፓውንድ (share capital of UK£300,000) ተመሠረተ። የታወር ትሬዲንግ ካንፓኒ ማኔጀሮች የነበሩ በሎንደን የኢትዩጵያ ኢንባሲ ሁለት ዲፕሎማቶች ከንፓኒውን መርተዋል። ታወር ትሬዲንግ ካንፓኒ በ2006 እኤአ ዓመታዊ ትርፍ መቶ ሃያ አምስት ሽህ ፓውንድ (UK£125,000) ፣በ2007 እኤአ መቶ ሁለት ሽህ (UK£102,000) በአጠቃላይ ዓመታዊ ትርፍ ከአንድ ሚሊዩን እስከ 1.2 ሚሊዩን ፓውንድ ይደርሳል። ታወር ትሬዲንግ ካንፓኒ ያሰገኘው ትርፍ ከኢፈርት አጠቃላይ እንቅስቃሴ አንፃር ገቢው ምንም ማለት አይደለም፣ ነገር ግን የውጭና ገቢ ንግድ አገልግሎት በመስጠት ትልቅ ሚና ተጭውቶል። ታወር ትሬዲንግ ካንፓኒ እስከ 2008 እኤአ ምንም ዓመታዊ ትርፍ ገቢ አልተገለጸም፣ታወር ትሬዲንግ ካንፓኒ፣ብሎም በ2010 እኤአ ካንፓኒው በታላቆ ብሪታንያ የካንፓኒዎች መዝገብ እንዲሠረዝ አድርገዋል።

" Tower Trading Company (called Senay Trading up to 1995) was incorporated in London in eptember 1993 with a share capital of UK£300,000. Trading in the company ceased several years ago, it does not appear in the EFFORT Company Profile (n.d.[2010a]), and steps were taken to close it down. The company is included here because documentation available from UK Companies House describes its shareholders as 'the trustees of EFFORT'. Former directors have included at least two diplomats at the Ethiopian Embassy in London. Latest accounts posted show annual profits of UK£125,000 in 2006, and UK£102,000 in 2007, on an annual turnover of between UK£1million and UK£1.2million. These figures would accord with the view that the company was not of great importance in the overall scheme of EFFORT operation, but provided useful facilitation of import/export activities. No annual returns have been submitted since 2008, and in March 2010 the company was removed from the UK Companies Register. The High Court in London reversed this decision in July 2010, in response to the petition of lawyers acting for Mulugeta Guade Mengiste and Addis International Trading, described by the court as 'creditors of Tower Trading Company.' There is no evidence that EFFORT owns other companies outside Ethiopia, and

interlocutors report that at present it does not. The prospect that it might do so in future, meanwhile, is explicitly not ruled out. ”

## የመዕድን ዘርፍ (Mining)

### {1} ኢዛና መዕድን ኃብት ኃ/የ/ግ/ማ (Ezana Mining)

ኢዛና ማዕድን ልማት ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማሕበር (Ezana Mineral Development Private Limited Company (EFFORT) በህወሃት/ ኢፈርት ባለቤትነት የተቆቆመ ካንፓኒ ሲሆን ዋና የበላይ ተቆጣጣሪዋ ወ/ሮ አዜብ መስፍን ስትሆን አታክልቲ አርዓያ ጀነራል ማናጀር ሆኖ፣ በትግራይ ክልል ውስጥ የተገኘውን 13 ቶን ወይም ፣13,000 ሽህ ኪሎ ግራም የወርቅ ማዕድን ለዓለም ዓቀፍ ጨረታ በማውጣት የካናዳዊያን የወርቅ ማዕድን ካንፖኒ ጋር ህወሃት/ኢፈርት በትግራይ ህዝብ ስም የሚዘረፈው የወርቅ ሃብት ነው፡፡ኢዛና ካንፓኒ 393.7 ሚሊዩን ብር የፕሮጀክት ወጭ 2017 ኪሎግራም ወርቅ በሁለት ዓመታት ውስጥ ለመማምረት አቅዶል፣ኢዛና በመዐድን ዘርፍ ለ106 ሠራተኞች የስራ እድል አንበሽብሾል፡፡ ለሙሰኛው ህወሃት/ ኢፈርት ‹‹የአዶላና የለገደንቢ ወርቅን የህወሃት መንግስት ለአላሙዲን ለጨረታ ሸጦል ከአራት አመት በኃላ በ 2018 እኤአ ስምምነቱ ያከትማል፡፡ህወሃት ያዘረፈንን የወርቅ ኃብት ከወዲሁ ስምምነቱን በድብቅ እንዳያድሱት የኢትዩጵያ ህዝብ፣ኢሣት፣የተለያዩ ድረ ጎፆች ከአሁኑ ህዝቡን ማሳወቅ ይጠበቅብናል፡፡ በአዶላና በለገደንቢ ወርቅ ማዕድን አካባቢ የሚኖሩ የኦሮሚያና የአማራ ህዝብም የልጅ፣የልጅ ልጆቻችሁ ኃብት በግፍ እየተዘረፈ እያያችሁ ከመኖር፣ ለኃብታችሁና ለነፃነታችሁ ፈጣሪ የሠጣችሁን አዱኛ አስነጥቃችሁ በድህነት እየማቀቁ መኖር እጣ ፈንታችሁ አይደለም፡፡ ከወርቃችሁ ኃብት የመጀመሪያው ተጠቃሚ የመሆን መብት አላችሁ፡፡In related news MIDROC Gold, one of the subsidiary companies of the MIDROC Technology Group, is at loggerheads with the Ministry of Mines over mining royalty payment. When MIDROC Gold bought the Legedembi gold mine in western Oromia for 172 million dollars in 1998 it entered into an agreement with the Ministry of Mines to pay five percent royalty fee to the ministry under the previous law. The agreement signed between the two parties is valid for twenty years.

በ1998እኤአ የለገደንቢ ወርቅ መዕድን በ172 ሚሊዩን ዶላር ለአላሙዲን በርካሽ በሙስና ሲሸጥ 98 እጅ ለሼኩና ለሚስታቸው ድርሻ ሲሆን 2 በመቶ የኢትዩጵያ ህዝብ ድርሻ ሆኖ መለስ ዜናዊ ቸበቸበው፡፡ የትግራዩን ወርቅ ለእራሱ ፓርቲ፣ ለኢፈርት ድርጅት ኢዛና አደረገ፡፡ የሚገርመው በሌሎች ሃገራቶች የወርቅ ማዕድን የኃብት ክፍፍል ለምሳሌ፣ በኢንዶኔዢያ 49 በመቶ እጅ የህዝብ ኃብት ነው፣በዚንባዌ 51 በመቶ እጅ የህዝብ ኃብት ነው፣በሞንጎሊያ 49 በመቶ እጅ የህዝብ ኃብት ሆኖ ቀሪው የኢንቨስተሩ ነው፡፡ በቻይናና በህንድ የወርቅና የተወሰኑ ማዕድናት በውጭ ሃገር ሰዎች ንብረት መሆን ሕጉ ይከለክላል፡፡

‹‹While it is not at all a new phenomenon, some authorities are trying to retain possession of their minerals. This was the third trend identified. The country also plans to introduce mandatory participation of a state-owned mining company. Other countries are doing the same. Indonesia has revealed a strategy aimed at capping external ownership of mines to 49 percent after 10 years. Zimbabwe has already started its 51 percent ‘indigenisation laws’. Mongolia has put a 49 percent limit on foreign ownership of strategic mines. China and India have constraints on foreign ownership of certain minerals. Changes to ownership laws can have a major bearing on the prize miners anticipate receiving for their risk.›› Source:-Resource Nationalism – Risky For Africa’s Economic Growth-November 2, 2013 ventures-africa Economic development, Economics.

**የተፈጥሮ ማዕድን ብሄራዊ ሪፖርት**
**ለተባበሩት መንግስታት ኮሚሽን ለዘለቁታዊ እድገት THE UNITED NATION COMISSION ON SUSTAINABLE DEVELOPMENT (UNCSD) ኒው ዮርክ**
**የኢትዬጵያ ፌዴራል ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስትር**
**አዲስ አበባ ፣ህዳር 2009 እኤአ**

‹‹ከ1974 እስከ 1991 እኤአ በሃረራቱ የግል ኢንቨስትመንት በማዕድን ሃብት ዘርፍ ላይ አልነበረም፡፡ እንዲያውም የመንግስት ዘርፍ የሆኑ ኢንስቲትውሽንስ የሃረራቱን ማዕድን ሃብት የመፈለግና የማውጣት መብት ሙሉ መብት ነበራቸው፡፡ በ1991 እኤአ የፖለቲካ ለውጥ ምክንያት፤ አዲስ በገበያ መር የተቃኘ የኢኮኖሚ ፖሊሲ በሃገሪቱ ተዋወቀና ወጣ፡፡ በማዕድን ሃብት ዘርፍ፤መንግስት አዲስ የማዕድን ሃብት አዋጅ፣የማዕድን ሃብት ታክስ አዋጅ በማውጣት የግል ዘርፉን ባለሃብቶች በማዕድን ሃብት ዘርፍ የማዕድን አሰሳ፣ፍለጋና፣ልማት የስራ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ፈቀደ፡፡››

‹‹ የማዕድን ሃብት አዋጅ ቁጥር 52/1993፣የማዕድን ሃብት ደንብ ቁጥር 182/1994 እዲሁም የገቢ ታክስ አዋጅ ቁጥር 53/1993 አዋጅ በማውጣት የግል ዘርፉን ባለሃብቶች መዕዋለ ነዋያቸውን እንዲያፈሱና ለመሳብ ታቀደ፡፡ አዋጆቹ በየግዜው እየተሻሻሉና በዓለም ዓቀፍ ደረጀ ተፎካካሪና ለኢንቨስተሮች ተስማሚ እንዲሆን ተደረገ፡፡››

‹‹እስካሁን ድረስ በሃገሪቱ በከፍተኛ ደረጃ የወርቅ ማዕድን ምርት የለማበት የለገደንቢ የወርቅ ማዕድን ነው፡፡ ለገደንቢ በደቡብ አረንጎዴ ድንጋይ የቀለበት ክልል ሥፍራ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን 82 ቶን ወይም 82,000 ኪሎ ግራም የወርቅ ማዕድን ክምችት ይኖረዋል ተብሎ ይገመታል፡፡ አማካይ አመታዊ ምርቱ ደግሞ 3.6 ቶን ወይም 3,600 ኪሎ ግራም የወርቅ ማዕድን ይሆናል፡፡››

ይላል የኢትዬጵያ ፌዴራል ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስትር ለተባበሩት መንግስታት ኮሚሽን ለዘለቁታዊ እድገት (UNCSD) በፃፈው ደብዳቤ፡፡ በሌላ በኩል የሜድሮክ የወርቅ ማዕድን የወርቁ ክምችት መጠኑ 37,215 ኪሎግራም ነው ይላል፡፡ 44,785 ኪሎግራም የወርቅ ማዕድን ክምችት ልዩነት በሁለቱ ሪፖርቶች መኃል ይገኛል፡፡ አንባቢ ከዚህ ጥናታዊ ፁሁፍ በመነሳት ሁለቱንም ከድረ ገፆቹ እንዲያነቡ እንጋብዛለን፡፡ (http://www UNCSD _National report_November 2009.doc) ይህ መረጃ ከድረ ገፁ ላይ በመነሳቱ ከታች እንዲያነቡት እንጋብዛለን፡፡
(http://www MIDROC Gold Mine Pvt Ltd. Co. (MGOLD)

## NATIONAL REPORT ON MINING

To: - **THE UNITED NATION COMISSION ON SUSTAINABLE DEVELOPMENT (UNCSD), NEW YORK**
FROM: - Ministry of Mines and Energy Federal Democratic Republic of Ethiopia.
(Addis Ababa, November 2009)

Source :-(http://www UNCSD _National report_November 2009.doc)

*Between 1974 and 1991 private investment was not allowed in the mineral sector rather government institutions were given the right to explore and develop the mineral wealth of the country. As a result of the political change that took place in 1991, a new market oriented economic policy was introduced in the country. In the mining sector, the government promulgated a new mining proclamation and mining income tax proclamations to encourage the participation of private capital in mineral prospecting, exploration and development activity.*

*The Mining Proclamation No. 52/1993, Mining Regulations No. 182/1994 and Income Tax proclamations No. 53/1993 were issued to attract private investment. The proclamations were consecutively amended so as to be competitive internationally and in favour of the investors.*

*So far developed large scale gold mine in the country is the Lege-dembi gold mine, located in the southern greenstone belt region, being operated by private company with estimated reserve of 82 tons and an average annual production of 3.6 tons of gold.*

